# ማ ነው ሌባው? ማ ነው ሌባ ኣምራች?

ነፃነት የሌለው ህዝብ በጠላቱ እጅ እንደከብት እየተነዳ ከአገሩ የሚሰደድ ፣ በገዛ ምድሩ ርስቱን በሌላ ሰው እጅ እያየ ጭሰኛ ሆኖ በውርድትና በመረረ ሀዘን የሚኖር፣ በከብቱ በንብረቱና በመቃብሩ መሬት እንኳን የማያዝበት፣ ለዘሩ የሚተላለፍ ባርነትን ወስዶ የሚኖር ህዝብ ማለት ነው።

......ዶሮ እንኳን ጫጩቶችዋን ከኣሞራ ለማዳን ትጠነቀቃለች። ይህ ከሆነ በኣእምሮም በጉልበትም ብዙ ሺህ ጊዜ የሚበልጠው ሰው ከራሱና ከሃገሩ ጠላት ጋር ምን ያህል መታገል እንደሚገባው እወቁ...... ነፃነት በመጥፋቱ ከውርደት ላይ እንዳትወድቁ ለማድረግ የመጣውን ጠላት ለመዋጋት ህይወታችሁን ባታሳልፉ ክብሩ የቱን ያህል ይሆናል?

የከበረ ስማችሁ በልጆቻችሁና በወገኖቻችሁ ዘንድ ሲመሰገን በታሪክም ሲጠራ ይኖራል።ይህ ከሻለቃ በቀለ ወያ ታሪክ ሽፍራው መንገሻ የቀነጨበው ነው።

የኢትዮጵያ ህዝብ ጤፍ በ 1000 ብር እየገዛ አስመራ ጤፍ 500 ብር ተሸጦአል።ይህ የሆነው የጎጃም ጤፍ በሱዳን በኩል እየተጋዘ ነበር፣ ወደ ትግራይ እንዲሁ፣ ይህንን ሁሉ ሲያደርጉ የነበሩት እነማን ነበሩ? ኬላውን ሲያስከብሩ፣ ኮንትሮባንድ ንግዱን ሲቆጣጠሩ የነበሩ። የማን ወገኖች ናቸው? እሁንስ እነማን ናቸው ከሸንኩርት ንግድ ጀምሮ ያለውን ገበያ የተቆጣጠሩት? እንዳሻቸው የሚነዱት?

ኮንትሮባንዱን የሚጫወቱት፣ ኬላ ላይ ሆነው የሚቆጣጠሩትና ግብር እየጣሉ ሌላውን ሽባ የሚያደርጉት? ከዚህ በላይ ነፃነት ማጣት እለ? ይህ ከሆነ በቀለ ወያ ትክክል ብለዋል። ዘር ማንዘርን ለኢኮኖሚ ባርነት እሳልፎ መስጠት ማለት ይሕ ነው። ለዛሬ ፅሁፍ መነሻ ይሆን ዘንድ ይህን ካልኩ የመነሻው መጀመርያ ስለሆኑት ወይዘሮ ደግሞ የሚከተለውን ልበል።

መቼም ለዲያስፖራው ድህነት ቅንጦት እንደማይሆን እርግጠኛ ነኝ። በመጥበሻ ላይ እንኳን የሚጋገር ማራገብያ የምታክል የስንዴ እንጀራ እንኳን የለችም። ውድ ሆናለች።

ወይዘሮዋን ቤታቸው ሄጀ ያነጋገርኳቸው ከእምስት እመት በፊት ነበር።የሚኖሩበት ቤታቸው ወላልቋል። የቤታቸው መሰረት በመናጋቱ መዝጊያዎቹና መስኮቶቹ እይገጥሙም።ግድግዳው

ቀለም ካየ ከ 30 ዓመት በላይ ሆኖታል። በቤቱ ውስጥ ያሉት ቁሶች ይዞታቸው ተቀይሯል።ጠረጴዛና ወንበሮቻቸው ተሰባብረው በእራፊ ጨርቆች ታስረዋል። እግሮቻቸው መቆም ስላቃታቸው ጉድጓድ ውስጥ እንዲገቡ ተደርገዋል።የማብሰያ ቁሶች ጥላሸት ጠግበው ሲፈጠሩ የነበራቸውን መልክ ቀይረዋል። ሌማቱ ደርቋል፣ ቦሀቃው የቤት ቅራቅንቦ ማስቀመጫ ሆኗል።

በየግርግዳው ላይ የተሰቀሉት ቁጥርጥሮች መልካቸውን የቀየሩ፣ ጥላሸት የጠገቡ፣ ምናልባትም እንደተሰቀሉ ባሉበት ሁለት መንግስት የተፈራረቀባቸው ይመስላሉ። ወይዘሮዋን ማግኘት የፈለኩት ስለኑሮአቸው እንዲያጫውቱኝ ነበርና ባቀረብኩላቸው ጥያቄ መሰረት ጭጋግማ ፊታቸው ላይ ፈገግታ ቢጤ እሳይተውኝ ያጫወቱኝን ከማስታወሻዬ እንደወረደ የወሰድኩትን ላቅርብ።

የምተዳደረው ከቤት ኪራይ አበል በማገኘው ገንዘብ ነው። ሁለት ልጆቼን ቀይ ሽብር ወሰዳቸው። እንደውሻ ሞተው አገኘኋቸው። ልጅ ቀድሞ ወላጅ ያለጧሪ ብቻውን እየኖረ ሞት የሚመኝበት ዘመን ላይ ደረስን....ንጉሱ ከስልጣን ሲወርዱ ቤቴ ተወረሰብኝ። እቺው ያለችው ቤት ቀረችልኝ። 33 ብር እበል እለኝ። ያው እንግዲህ ዛሬ ድረስ በዚህችው ገቢ አለሁ።

ባለቤቴ ከሞተ በኋላ ጠላ ዳቦ እንጀራ ....እሰራ ነበር። ደከምኩና ተውኩት። እሁን ለነፍስ ያለ እየረዳኝ ቀን እገፋለሁ። የኑሮ ነገር ግራ ገብቶኛል። ጨለማ ውስጥ ቁጭ ብዬ ጭለማ ውጦኛል።በተንኮታኮተው ቤት ውስጥ ሆኜ ከእንደበታቸው የሚወጣውን የከፋ የድህንት ቃል ስሰማ ቀስ በቀስ ወደመቃብር የምወርድ ያህል ውስጤ ሲርድ ሰማሁት። የስብሀት ማስታወሻ ትዝ እለኝ። ዘነበ ወላ ያጠናከረው የስብሐት ማስታወሻ ድህነትን እሳምሮ ገልፆታል።እርጎ ውስጥ ምናምኑ ገብቶ ምናምኑን እውጥቶ መጠጣት ለምንጠየፍ፣ እርጎ ጠጥቶ ያስመለሰውን ከአፍ ተቀብሎ መልሶ ለምግብነት ማዋል ድህነትን አምኖ ከመቀበል ውጭ ሌላ አማራጭ የለም።በዚህ ስሜት ውስጥ ሆኜ ፖለቲከኞቹን እሰብኳቸው። እንመራሀለን ብለው በሀይል የተፈናጠጡበት ያገራችን መሪዎች እንዲህ ያለውን ህዝብ እንደሚመሩ ለእፍታም መዘንጋታቸውም ከድህነት በላይ የሀገራቸን እሳሳቢ ጉዳይ ሆኖ ታየኝ።

ስጋ ከሌለው ህዝብ ላይ ከእጥንቱ እየጋጡለት ተደላድለው ለመኖር የወሰኑ የአገሬ መሪዎች ጭካንያቸው ሳይሆን ከጊዜና ከታሪክ መማር እለመቻላቸው ደግሞ ነገ የሚሆነውን ሳስብ በእጅጉ የሚያስጨንቅ ይሆናል “ ዋናው ጠላታችን ድህነት ነው ከድህነት በላይ ጠላት የለንም ” እቶ መለስ ደጋግሞ የሚናገሩት የፓርቲያቸውና የሳቸው ነጠላ ዜማ መጨረሻው በኑሮ ውድነት መጠበስ መሆኑ ለሳቸውም ሆነ ለፓርቲያቸው የ 20 እመት የእገዛዝ ዘመን ውጤት ኩራት ከሆነ እነሱው ይኮፈሱበት።

ስጋ ገዝተው ያውቃሉ? እልኳቸው። እላውቅም የምን ስጋ ቢላ ሲፏጭም ሰምቼ አላውቅም፣

ሲሉ መለሱልኝ። ቤታቸው ተፈጭቶና ተቦክቶ እያውቅም፣ ለ 20 አመታትም ጋግረው እያውቁም። እኚህ ሴት ምርጫ ሲመጣ ኢህአዴግን ምረጡ ይባላሉ። የእኚህ ሴት ለውጥ የመፈለግ መብት እንኳን እይከበርም።ልብስ የሚባል ነገር ገዝተው አያውቁም። የሚተኙበት አሮጌ አልጋ ልብስ የለውም። ብርድልብሱም ቢሆን አርጅቶ ነትቧል። የውስጥ ልብሶቻቸው አልቀዋል። የውስጥ ሱሪ የሚባል ነገር ተረስቷል። ወይዘሮዋ ደጋግመው የፈጣሪያቸውን ስም እየጠሩ የሚናገሩት ቢኖር አይናቸውን  ያዝ ከሚያደርጋቸው በቀር ሙሉ ጤነኛ መሆናቸውን ነው።

የወይዘሮዋ ዘግናኝ ህይወትና ኑሮ ጉዳይ እዚህ ላይ ላቁምና በቅርቡ በኢትዩጵያ የኑሮ ውድነት የከፋ ደረጃ መድረሱን ተከትሎ የችግሩ ምንጮች የወሰዱትን የመፍትሄ ርምጃ በተመለከተ የበኩሌን ልበል።

በኢትዩጵያ ኑሮ ተቃጥሏል ፣ኑሮ ያልፈጀው የለም፣የኑሮ ክፋቱ ሆዳቸውን ብቻ ሳይሆን ስብእናቸውን የገደለባቸው ኢትዮጵያውያን በቁጥር የሚገለጹ አይደሉም። በሌላ በኩል ደግሞ ሊታመን በማይችል ሁኔታ በየእለቱ የሚፈጠሩ የትላንት ውርጋጦች የዛሬ ባለሀብቶች |ጥቂት አይደሉም፣ እናም ኢትዮጵያ ለብዙሃኑ ሲኦልና መራራ ፣ለጥቂቶች ደግሞ ገነትና ማር ሆናለች፣ ገና ትሆናለች፣ አያያዝዋ እንደዛ  ይመስላል።

የዛሬው ባለሀብቶችን ከደርግ የተቀበልናቸው ሳይሆኑ እኛ የፈጠርናቸው በመሆኑ ኩራት ይሰማኛል በማለት አቶ መለስ ዜናዊ ሲገልፅ፣ እናንተ የምትበሉት ያጣችሁ ዜጎች እኛ ኢሃዲጎች የፈጠርናችሁ ናችሁ፣የሚለውን ሀቅ ውጠውት ዝምታን መርጠዋል፣ ነገር ግን ለደሀው አሳቢ በመምሰል "ሌባ ነጋዴዎችን " የመመንጠር ዘመቻ መጀመራቸውን ይፋ አድርገዋል።

ማነው ሌባው? ሌባ ነጋዴን የፈለፈለውስ ማነው? የዛሬ ጽሁፌ መነሻና መድረሻ ይሄው ግራ እያጋባ ያለው የኢትዮጵያ መሪዎችና የአመራራቸው ድራማ ይሆናል፣ ለዚህ በኢትዮጵያውያን ላይ ለሚሰራ ድራማና ትያትር ግን እርእሱን ራሳችሁ ምረጡ።

## ማ ነው ሌባ? ሌባ ነጋዴስ?

በየትኛውም መመዘኛ የቅንጅት ፖለቲካ መዘዙ ገና ተጀመረ እንጂ አላለቀም፣ የቅንጅትን ፖለቲካ ተከትሎ አቶ መለስ የቋጠሩት ቂም በቅንጅት አመራሮች እስርና ይቅርታ አጀንዳው የተዘጋ የሚመስላቸው ካሉ የዋህን ብቻ ናቸው። ጨካኝ ፖለቲከኛና ፈጣን እርምጃ የሚወስድ አመራር ጠፍቶ እንጂ ቅንጅትን ለመደገፍ ሰላማዊ የወጣው ህዝብ የአዲስአበባን እምብርት ባጥለቀለቀበት በዚያ እለት ጫወታውን በመቀየርና ለጠቅላይ በመጫወት፣ የወያኔን አጀንዳ መቋጨት ከወያኔ ጭካኔ አንጻር ደግነት እንጂ የጨዋታን ህግ በመቀየር የሚያስወነጅል አልነበረም። ግንቦት 7 ቀን 1997 ዓመተ ምህረትም ምርጫ የሚደረግበት እለት ሳይሆን የአዲሱ መንግስት ካቢኔ በይፋ ስራውን የሚጀምርበት እለት በሆነ ነበር ። በነበር ቀረ። ከዚያ በኋላ ነው እንግዲህ ከተሸናፊነት ወደ ጉልበት አሸናፊነት  በመሸጋገር ከቂም ቋጠሮ እየተፈታ በየጊዜው ለበርካቶች ስቃይ የሚ ሆነው አጀንዳ የሚመረጠው።

የወያኔ መሪዎች በተለይ አቶ መለስ ያችን ቀን ሲያስታውሷት ራሳቸውን የት ፈልገው እንደሚያገኙት ሲያስቡ ድንጋጤያቸው የኤሌትሪክ ንዝረት ያክል ውስጣቸውን አራግፎት ስለሚወጣ ይህ ስሜት በመጣባቸው ቁጥር ሁሌም የሚያደርጉት የቅንጅትን ያልተዘጋ ፋይል ማገላበጥ ነው፣ እድሜ ለባንዳዎች፣እድሜ ለፋይል አቀባባዮች!!!

ከቅንጅት ፖለቲካ በሗላ ወያኔ በየዘርፉ ግምገማ አካሂዶ ነጥሎ ያወጣቸውን ክፍሎች ለቅንጅት ማበብ  ዋና ባለጉዳዮች በመሆናቸው እነዚህን ክፍሎች በየደረጃው “ የመቁረጥ ” ወይም ከጨዋታና ከሲስተም ውስጥ የማስወጣት እስትራቴጂ መንደፉን የምናውቅ እናውቃለን።

የመጀመርያው ተጎራጅ ወይም ተቆራጭ የመንግስት ሰራተኛው ነው፣ የዛሬው ተረኛ ደግሞ ነጋዴው በመሆኑ እዚሁ ላይ አተኩራለሁ፣ማነው ሌባው ለሚለው ጥያቄው ምላሽ መስጠት የሚቻለውም ይህው የነጋዴው ጉዳይ ሲነሳ ነው።

584 የሚጠጉ ተጽእኖ ፈጣሪ የተባሉ ነጋዴዎችን አቶ መለስ አነጋገሩ እየተባለ የሳቸውን አንደበት በሚያራግቡ የሀገር ውስጥ ቅልብና ቅምጥ ጋዜጠኞች ሲስተጋባ ተፅእኖ ፈጣሪ የሚለውን ቃል እንዳሰምርበት ተገደድኩ።እነማናቸው ተፅእኖ ፈጣሪዎች? ቅምጦቹና  ቅልቦቹ የሀገሬ ጋዜጠኞች  በዝርዝር ይንገሩን፣ አቶ ወይም ወሮ እገሌ ናቸው ተጽእኖ ፈጣሪ ወይስ ኤፈርት፣ ትራንስ፣ ጉና፣ አምባሰል፣መስፍን ኢንጂነሪግ፣ ሜጋ፣ ቱምሳ ኢንዶመንት፣ቢፍቱ፣ጥረት፣ማህበረ ወልዳ፣አነስተኛ የንግድ ተቋማት፣ በግለሰብ ስም ተከፍተው በተዘረፈ የፓርቲ ሀብት የሚነግዱት  እነ እንቶኒዎች፣  እነ የአንድ ቡድን አባላት፣ ወይስ ተራው ነጋዴ?

የሀገሬ ሰው መተረት ያውቃል፣ ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ እንዲሉ! ለመሆኑ እነማን ከቀረጥ ነጻ ያስገባሉ? እነማን ኮንትሮባንድ ይነግዳሉ? እነማን ኬላውን ይጠብቃሉ?እነማን ግብር ይተምናሉ? እነማን ናቸው አየር በአየር የሚነግዱት? እነማን ናቸው የቻይና፣ የህንድ ፣የብራዚል ሀብታም ከፊት ለፊት አቁመው በሲሚንቶ ንግድ ገንዘብ የተራጩት?ገንዘብ የጠገቡት? አረ ጉድ! እናስ ማነው ሌባ ነጋዴ? ማነው ተጽእኖ ፈጣሪ? በህወሀት አምሳል ተጠፍጥፈው የተሰሩ ነጋዴዎችስ?

የገቢዎችና የጉምሩክ ባለስልጣን ምክትል ዳይሬክተር አቶ ገብረ ዋህድ ገብረጊዮርጊስ “ ኑሮ ውድነቱ ጉልበተኛና ቀማኛ በመፍጠር፣ አገር ችግር ውስጥ እንዳትገባ ምክንያት ሊሆንና ሰላማዊን ኑሮን ሊያደፈርስ ይችላል”በማለት መናገራቸውን  እንደ ኤ.አ አቆጣጠር ታህሳስ 19 2011 በወጣው ሪፖርተር ጋዜጣ ላይ ሳነብ አፌን የረጋ ደም የሞላው ያህል ተሰማኝ፣ምክንያቱም አቶ ገብረዋህድ ስለሌባ ነጋዴ መግለጫ ሲሰጡ ፣ ለአገር ሲሰጉ መስማቴ የሌባ አይነ ደረቅ .....ሆነብኝና ነው፣በዚሁ ጋዜጣ ላይ የንግድ ሚኒስቴር ዴኤታው አቶ አህመድ ቱሳ “ ባልተገባ የዋጋ ጭማሪ በቱኒዝያ  የተፈጠረው አይነት ችግር በኢትዩጵያም ሊደገም አይገባም|“ ያሉትን ስመለከተው እንደቱኒዚያው መሪ የወያኔ መሪዎች አገር ጥለው ቢወጡ የሚያዝን ያለ

መስሏቸው ይሆን ስል " የዋህ" ብዬ ጠራ ኋቸው።

ወደ ቅንጅት መዝገብ ልመለስ፣ቅንጅት በአጭር ጊዜ በህዝቡ ሁሉ ተቀባይነት አግኝቶ ሀገር ሲያነቃንቅ በግምባር ቀደምትነት ኢጋዥ የነበሩት ነጋዴዎች ሲሆኑ በሁለተኛ ደረጃ የአዲስ አበባ ታክሲ ሹፌሮችና የታክሲ ባለንብረቶች ናቸው በሚል ተፈርጀዋል።በታክሲ ትራንስፖርት ዘርፍ ወያኔ ያሰበውን አዲስ የመቁረጥ ስልት ወደፊት እመለስበታለሁ፣ ለዛሬ ግን ትኩረቴ በነጋዴዎች ዙርያና ነጋዴዎችን ለማጥፋት የተጀመረው ዘመቻ እንዴት እንደተቀነባበረ ላብራራ።መቼም ወያኔን የሚያውቅ ሁሉ የወያኔ ተንኮልና የአቶ መለስ የተንኮል እርምጃ የሚጠፋው ያለ አይመስለኝም።ህወሀት የፈለፈላቸው ከህዝብ በተዘረፈ ሀብትና ንብረት በእግራቸው ቆመው ዛሬ ወደ ሞኖፖሊነት የተዘዋወሩት የንግድ ኩባንያዎቹና ሽሪኮቹ ከቀረጥ ነጻ በማስገባት፣በየትኛውም የንግድ ዘርፍ በመሳተፍ፣በስራ ፈጠራ ስም በርካታ ድሆችን በመመልመል ገበያውን ከተቆጣጠሩት አመታት ቢያልፉም፣ ቅንጅት ካበበበት ጊዜ ጀምሮ በነጋዴው ህብረተሰብ ላይ የቂም እርምጃ ለመውሰድ ሁኔታዎች ሲመቻቹና ኢጋጣሚዎች ሲጠበቁ ነበር።ታድያ ዛሬ የሚሆነው ይህንኑ ነጋዴ ለኑሮ ውድነቱ ብቸኛ ተጠያቂ በማድረግ ከህዝብ ጋር ካጣሉት በኋላ እኛ ደርስንልህል የሚል መዝሙር በመያዝ አቶ መለስ ብቅ አሉ። የዋጋ ንረቱን የፈጠሩት የራሳቸው የህወሐት ልጆችና ደንገጥሮች ሆነው ሳለ ሌላው ነጋዴ በነሱ ፍጥነት የተወዳዳሪ ስሜት ውስጥ ገብቶ ከእነሱ እኩል ሲሸጡና ሲለውጥ ቆይቶ ቀደም ሲል በተጠመደለት ወጥመድ ውስጥ በፍቃደኝነት እየገባ እንደነበር አልተረዳምና ዛሬ የቆረጣው እርምጃ ሲጀመር ተንጫጫ።

ዳቦ ያረረበት ህዝብም መንግስትን በጥርጥሮሽና በሆዱ ጎሽ ይለው ጀመር። አንድ ኪሎ ስጋ በ 100 ሲገዛ የነበረ ህዝብ አንድ ኪሎ ስጋ በ 50 ብር ብላ ብለው አቶ መለስ ሲነግሩት የበሬ ዋጋ ስንት ሊሆን ነው በሚል በቁሙ በሬ የሚገዛበትን ዋጋ አስቀድሞ መተመን ይቻላል? ብሎ ሳያስብ አጨበጨበ።ይህ የተፈለገውና የተወጠነው የህዝብ ድጋፍ ማግኛ መንገድ ለጊዜው ወያኔዎችን ቢያስደስትም ችግሩ ውሎ ሳያድር ታየ።የቄራዎች ድርጅት ስራ አስኪያጅ የማርደው በሬ አጣሁ፣ የሰራተኞቼ ጉዳይ አሳስቦኛል ሲል መጮህ ጀመሩ።ይህ አንድ ምሳሌ እንጂ ዝርዝር ማሳያ አይደለም።ጥቂት የማይባል የዋሆች፣ የራሱን አጥንቱ ላይ ያለ ስጋ ባገዛዙ ጅቦች እየሸገነጠለ እያለ፣ በአንድ ኪሎ ስጋ ዋጋ መቀነስ ተደስቶ ከበሮ ሲመታ፣ ቅምጥና ቅልብ ጋዜጠኞች ይህንኑ በስካር መንፈስ ሲያነበንቡት ጉድ ከማለት ውጭ ሌላ ምን ይባላል።

ስለጋዜጠኞች ካነሳሁ አንድ ነገር ልብል፣ የኮንዶምኒየም ቤት ተመረቀ የሚል ዜና ሲያነቡ በቴሌቪዥኑ መስኮት ወጥተው እቃ እየደረደሩ ማሳየት የሚቃጣቸው፣በትረ በረከትን ለማርካት አፍንጫው እየተነፋፋ፣ አረፋ እየደፈቁ ወሬ የሚያስተጋቡት ጋዜጠኞች የታያቸው ባለሀምሳ ሁለት ብሩ ስጋ ለጥሬ አይሆንም ምን ይሻላል? እያሉ ለጥራትና ለጮማ ቅድሚ ሰጥተው ሲጨነቁ እንደነበር አንድ ወዳጄ በማይታመነው ሞባይል አጫውቶኛል።

ከትንሽ እስከትልቅ የንግድ ስራ ውስጥ በመሳተፍ ያስመጪነቱንና የላኪነቱን ዘርፍ ሙሉ በሙሉ ያለተቀናቃኝ የተቆጣጠሩት ፣ለማስመሰል ታማኝ አሽከሮችን ከፊት ለፊት በማቆም ከጀርባ ሆነው በሌላ ብሄር ስም እየነገዱ ዋጋ በመስቀል ህዝቡን በኑሮ ውድነት ያሰከሩት እራሳቸው

ሆነው ሳለ ሌባ ነጋዴን እንመነጥራለን፣መንግስት ጣልቃ ይገባል፣ህዝብ ሲራብ መንግስት ዝም አይልም፣ አቶ መለስ ከትእግስት በኋላ የህዝብን ጉሮሮ ሊያራሱ ተነስተዋል፣ በሚል እየተስተጋባ ያለ የተለመደው ነጠላ ዜማ ፣ወያኔ በጥቁር መዝገብ የከተባቸውን ነጋዴዎች ከህዝብ ነጥሎና አጣልቶ የማጥፋት እርምጃ የመጨረሻው መጀመርያ መሆኑን እንድንረዳው ግድ ይላል።አንድ ሰሞን ዘይት ጂምላና ችርቻሮ አስመጪዎች ድርጅት ( ጅንአድ) ለማስረከብ የተፈራረሙት ሁለት ግዙፍ ኩባንያዎች ባለቤቶቹ የስልጤ ብሄረሰብ አባል ቢሆኑም ግብር የሚያስገቡት ለማን እንደሆነ ለማታውቁት ወደፊት በዝርዝር አወጋችኋለሁ።በሁሉም አይነት የንግድ ዘርፍ ለወያኔ እነዲነግዱ የተመረጡ የሌላ ብሄር አባላት (ፍሮንት ሜን) ላስመሳይነት የተሰፋላቸውን ጥብቆ ለብሰው ከወያኔ ባለስልጣናት ጋር ከፍተኛ ግምት ያለው የንግድ ውል በከፍተኛ ገንዘብ ይፈራረማሉ፣ ቅምጦቹና ቅልቦቹ ጋዜጠኞች ይህንኑ ስምምነት በየደረጃው ያስተጋቡታል።

አቶ መለስ አሁን የጀመሩትን እርምጃ አጠናክረው እንደማይገፉበት ቢታወቅም ኢህአዲግ የጠላቸው ነጋዴዎችን በልተው ሲጨርሱ ወደትራንስፖርቱ ዘርፍ ይዞራሉ። ይህን ጊዜ የነጋዴዎቹን ጉዳይ እርግፍ አድርገው እሳቸው ለፈጠሯቸው ባለሀብቶች እንደሚለቁት ጥርጥር የለውም…" አሁን ያላችሁት ሀብታሞች ከደርግ የተረከብናችሁ ሳትሆኑ እኛ የፈጠርናችሁ ናችሁ " ያሉትም ለዚሁ ይመስለኛል፣

ወይዘሮዋን ላስታውሳችሁ፣ መሸመትና መብላት የሚባለው አለምአቀፋዊ ቁዋንቛ ለሳቸው ተረት ሆንዋል።በአስማት ይነጋና በአስማት ይመሸላቸዋል፣እንደዚህ ኖረው ኖረው የፈለጉትን የመምረጥ መብታቸውን ተነፍገው ሞቱ። ተመልሼ ልጠይቃቸው ስሄድ ቤታቸው ፈርስዋል ፣ኢንቨስትመንት መሆኑ ነው፣በሳቸው ቤት ፍራሽ ላይ ባለቀኖች ህንጻ እየገነቡበት ነው፣ የእኚህ አይነት እናቶች ነፍስ ይጮህል ፣ከመሬታቸው የተባረሩ አባወራዎች ላይ የተፈጸመው ግፍ ተራራ አክሏል፣ የእነዚህ አይነት ህዝቦች የታቀፈችን ሀገር እየመሩ ለራሴ ተመችቶኛል በሚል በጭካኒያዊ የሰባ አስተሳሰብ ከበሮ እየመቱ መኖር እስከመቼ ይቀጥል ይሆን?የቀን እንጂ የሰው ጀግና የለውም የተባለው እንዲሁ አይመስለኝምና ለወያኔ መሪዎችና ባንዳዎች ስጋት ዶክተር መራራ ከተናገሩት አንድ ትልቅ ጉዳይ ልመርቅ" የሚበላው ያጣ ህዝብ መሪዎቹን ይበላል "ነበር ያሉት፣ ምን ቀረ? በቀን ሶስቴ ትበላለህ ተብሎ ከ 20 አመት በፊት የተነገረው ህዝብ አንዴም መብላት አቃተው።

በዋዜማው ላይ ነን መሰለኝ ጉምሩክን እንደኮሶ ተጣብተው የኖሩና በሚሊዩን የሚቆጠር ገንዘብ የሰበሰቡ የወያኔ አባል የቱኒዚያን መንግስት ምሳሌ ማጣቀስ ጀምረዋል፣ የንግድ ሚኒስትሩም የቱኒዚያን ፕሬዝዳንት ስደት እያወጉን ነው፣ ስደተኛው የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የቱኒዚያን ህዝብ አመጽና የፕሬዝዳንቱን ስደት እያሳየን ነው፣ወያኔ ሲጨንቀው ማጣቀስ ይወዳል፣ የሰሞኑ ጥቅሱ ይህው የኑሮ ውድነቱና መዘዙ ነው።አይናቸውን በጨው ያጠቡ መሪዎች አገር ጥለው መሰደድ ቀርቶ ሌላም የከፋ አደጋ ቢደርስባቸው ማን "ውይ!" ብሎ ሊያዝን? እሰይ እሰይ ደስ ማለቱ ተብሎ ይዘፈን ይሆን እንጂ! ላለፉት 20 አመታት ማንነቱ፣ የማንነቱ መገለጫ፣ ሉአላዊነቱ፣ክብሩ ተገፎ ተገፎ በመጨረሻ በችጋር እየተጠበሰ ያለ ህዝብ ሀዘን አይሰማውም!!! ወደጉዳዩ ልመለስና

ማነው ሌባ ነጋዴ? ማን ነው ኑሮን ያናረው? ማነው ሌባ? ማነው ተቀባይ? ጥያቄዬን መልሱልኝ።

ቀኝ እጅ የሚሰራውን ግራ እጅ ካየ

ግራ እጅ የሚሰራውን ቀኝ እጅ ማየቱ ችግር ከፈጠረ

አንዱ ሌላውን እያየ መኖር የለበትምና

የግራን ወይም የቀኙን እጅ እንቆርጠዋለን፣ በማለት ቡና ላኪዎችን ሲያነጋግሩ የፎከሩት አቶ መለስ፣ የትራንስፖርት ዘርፉን 60 በመቶ የተቆጣጠሩት የአንድ ብሄረሰብ አባላት ናቸውና ዘርፉን ከእነዚሁ የፈረደባቸው ብሄሮች እጅ ለመንጠቅ የዱባይን ታክሲ ሲስተም ያጠናው ህንዳዊው ኤክስፐርት ስላቀረበው የመፍትሄ ሀሳብ፣ ስለገጀራ ገበያ፣ ስለገጀራ ምርትና የገጀራ ምርት ቁጥጥር በቀጣይ ጊዜ ወስደን እንነጋገራለን።

አሁንስ ሌባው ማነው?

ሞገስ ተፈራ ......22/01/2011